መጽሀፍ IV

ምን እንደሚጠብቁ

# የእኔ የጥገኝነት ማመልከቻ



# እንኳን ደህና መጡ!

## ይህ ታሪክ ልክ እንደ እናንተ ባሉ በአራት ወጣቶች ዙሪያ ያጠነጥናል።

ረዥም ጉዞ ካደረጉ በኋላ ወደ አውሮፓ በሰላም ደርሰዋል።
አንዳንዶቹ ወጣቶች ብቻቸውን የመጡ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው ጋር መጥተዋል።
እነዚህ ወጣቶች ብዙ ጥያቄዎች አሏቸው — እና በሚኖሩበት ቦታ በሚሠሩ ሰዎች እርዳታ ያገኛሉ።

## ይህ ታሪክ እርስዎንም ሊረዳዎት ይችላል!

ይህንን ይማራሉ፡

- የጥገኝነት ሂደት ማለት ምን ማለት እንደሆነ
- ምን እንደሚጠብቁ
- ከባለሥልጣናት ጋር መተባበርና መሳተፍ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ
- እርስዎን ሊረዳዎ የሚችል ማን እንደሆነ
- ስለ መብቶችዎ

ታሪኩን ማንበብ ይችላሉ፡

- ብቻዎን
- ከጓደኛ ጋር
- እዚህ ከሚሰራ አንድ ሰው ጋር

## ጊዜ ይውሰዱ። ማቆም እና በኋላ ወደ ታሪኩ መመለስ ችግር የለውም።

አንድ ነገር ለመረዳት አስቸጋሪ ከሆነ፣ እንዲያስረዱዎት ይጠይቁ ።
ሞግዚትዎ፣ ማህበራዊ ሰራተኛዎ ወይም ጠበቃዎ ሊረዱዎት ይችላሉ።

## በታሪኩ መጨረሻ ላይ የሚከተሉትን ያገኛሉ፦

- አካባቢያዊ መረጃ ያለበት ገጽ
- አዝናኝ ጥያቄዎች
- ለጥያቄዎች የሚሆን ቦታ እና ጠቃሚ የእውቂያ መረጃ

ብቻቸውን ለሚመጡ ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች ሞግዚት ይመደባል። በአንዳንድ አገሮች ሞግዚቱ ተወካይ ተብሎም ይጠራል።

እንዲሁም፣ በአንዳንድ አገሮች ጥገኝነት መጠየቅ ደግሞ ዓለም አቀፍ ጥበቃ መጠየቅ ተብሎ ይጠራል።

! በመጨረሻም፣ የሚቆዩበት የመቀበያ ተቋማት የሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች በሙሉ ነጻ መሆናቸውን ይወቁ። አንድ የሥራ ባልደረባ ገንዘብ ከጠየቀዎት፣ የሚተማመኑበትን መኮንን ወይም ሞግዚትዎን ያነጋግሩ።

# በታሪኩ ውስጥ ያሉ ገጸ-ባሕርያትን ይተዋወቁ

## መሐመድ (Mohamed)

እድሜዬ 17 ዓመት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ደስተኛ ነኝ። በተቻለኝ ጊዜ ሁሉ ጓደኞቼንና ቤተሰቦቼን መርዳት እወዳለሁ። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ብቻዬን የመጣሁ ሲሆን አያቴን እየፈለግኩ ነው። ሥራ ለመጀመር ጉጉት አለኝ።





## አህመድ (Ahmed)

እድሜዬ 15 ዓመት ነው። እናታችን ከሞተች ወዲህ እኔን ስትንከባከበኝ የነበረችው ትልቁ እህቴ ጃስሚን ጋር አብሬ መጥቻለሁ። ከጓደኞቼ ጋር መዝናናት እና አዲስ ጓደኞች ማፍራት እወዳለሁ። በተቻለኝ ፍጥነት ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እፈልጋለሁ። በአሁኑ ጊዜ እዚህ ያለውን አካባቢያዊ ቋንቋ እየተማርኩ ነው።

## ጃስሚን (Jasmine)

እድሜዬ 24 ዓመት ነው። በተቻለኝ መጠን የምንከባከበው ከወንድሜ አህመድ ጋር አብሬ መጥቻለሁ። በቅርቡ ነው የደረስነው እና ለተወሰነ ጊዜ አውሮፓ ውስጥ ከኖረው ከአጎታችን ጋር ለመቀላቀል እየሞከርን ነው። ስፖርቶችን እወዳለሁ እና እግር ኳስ በመጫወት በጣም ጎበዝ ነኝ።



## አዳም (Adam)



እድሜዬ 9 ዓመት ነው። እዚህ ያለሁት ብቻዬን ነው። ለጊዜው ላለመናገር ወስኛለሁ። እዚህ ከመድረሴ በፊት ብዙ መጥፎ ነገሮች አጋጥመውኛል። እንደገና ለመናገር ጊዜ ያስፈልገኛል። ግን ብልህ ነኝ እና ሁሉንም ነገር እረዳለሁ። በጣም ጥሩ አድማጭ ነኝ እና ትምህርት ቤት መሄድ እፈልጋለሁ። እስካሁን ያፈራኋቸውን አዳዲስ ጓደኞች በሙሉ እወዳለሁ።



## ወይዘሮ ኢነስ (Ms Ines)

እኔ በዚህ የመቀበያ ማዕከል ውስጥ የምሰራ ሞግዚት ነኝ። ጥገኝነት የሚጠይቁትን ሁሉንም ህፃናትና ወጣቶች በተቻለኝ መጠን ለመርዳት እሞክራለሁ። ምግብ ማብሰል እወዳለሁ እና ሁሉም ሰው ሥራ ላይ ሲሆንና ንቁ ሲሆን ደስ ይለኛል። ስፖርት ሁላችንንም በአካልም ሆነ በአእምሮ ጤናማ ያደርገናል።

## አቶ ፍሬድ (Mr Fred)



እኔ የሕግ አማካሪ ነኝ፣ ይህም የጠበቃ ዓይነት ነው። እዚህ ከብዙ ጥሩ ስልጠና ካገኙ ባልደረቦች ጋር አብሬ እሰራለሁ። ለሁሉም የጥገኝነት ጠያቂዎች በሕግ ጉዳዮች እና በጥገኝነት ማመልከቻቸው ላይ መረጃና ድጋፍ እሰጣለሁ። መልዕክት ያላቸው ባለቀለም ቲ-ሸርቶችን መልበስ እወዳለሁ።

ይህ ታሪክ ከመታተሙ በፊት አንብበው በጣም በሚያምር ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የረዱትን ወጣት የጥገኝነት ጠያቂዎች በሙሉ ከልብ እናመሰግናለን።

የዋና ገጸ-ባሕርያትን ስሞች ለመምረጥም ረድተዋል።

እንዲሁም ከታዳጊዎቹ ጋር ውይይቶችን በመደገፍ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ላደረጉ በማልታ እና በኔዘርላንድስ ለሚገኙ ባለሥልጣናት ምስጋና ይገባል።


ግቡ!
ASYLUM


ሰላም አቶ ፍሬድ፣ ስለ ጥገኝነት ሂደት የበለጠ ማወቅ እንፈልጋለን!
... እንዲሁም በግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልስ ወቅት ምን እንደሚሆን...
... እና ውሳኔ ከተሰጣችሁ። በኋላ...
ዋው፣ ብዙ ጥያቄዎች አላችሁ! አጠቃላይ እይታ እሰጣችኋለሁ። ለእናንተ ሁኔታ ልዩ የሆኑ ዝርዝሮችን ለማግኘት፣ እንደገና ኑና የበለጠ እነግራችኋለው።
ASYLUM


ASYLUM
አገራችሁ ለእናንተ። ደህንነቱ የተጠበቀ ስላልሆነ መመለስ ካልቻላችሁ፣ ጥገኝነት መጠየቅ ትችላላችሁ።
ሁሉም ሰው ጥገኝነት የመጠየቅ መብት ቢኖረውም፣ ሁሉም ሰው ጥበቃ አያገኝም።
ጥበቃ ስትል ምን ማለትህ ነው?
ጥበቃ ማለት ጥገኝነት የጠየቃችሁበት አገር ውስጥ እስከሚያስፈልጋችሁ ጊዜ ድረስ መቆየት ትችላላችሁ ማለት ነው።
ጥበቃ ማግኘታችሁ ወይም አለማግኘታችሁ የሚወሰነው የትውልድ አገርዎ ለእርስዎ ደህና አይደለም ብለው በሚያምኑበት ምክንያት ላይ ነው። ለምሳሌ...
በሚከተሉት ምክንያት ለመመለስ የሚፈሩ ከሆነ፡-
- በቆዳዎ ቀለም ምክንያት
- በሃይማኖትዎ፣ በባህልዎ ወይም በሚያደርጓቸው ልማዶች ምክንያት
- በብሄር ቡድንዎ ምክንያት
- በእርስዎ ወይም በቤተሰብዎ ፖለቲካዊ አመለካከት ምክንያት
- በሚያፈቅሩት እና አብረው መሆን በሚፈልጉት ሰው ምክንያት
- እርስዎ ያሉበት ግን ተቀባይነት የሌለው ቡድን ምክንያት


... በተጨማሪም፣ በአገራችሁ ውስጥ ጦርነት ካለ ወይም ከተመለሳችሁ ሌሎች ዓመፅ ሊያጋጥማችሁ ከሆነ ጥበቃ ልታገኙ ትችላላችሁ።
ሰዎች ከአገራቸው እንዲሰደዱ የሚያደርጉ አንዳንድ ሁኔታዎች እነዚህ ናቸው።
ስለዚህ፣ ደህንነቴ የተጠበቀ ካልሆነ እና አገሬ ሊጠብቀኝ ካልፈለገ ወይም ካልቻለ፣ ጥገኝነት መጠየቅ እችላለሁ?
በትክክል!
በአንዳንድ አገሮች ለሴት ልጅ አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ሴት ልጆች በነጻነት መንቀሳቀስ አይችሉም፣ ከትምህርት ቤት ሊታገዱ ወይም ለጋብቻ ሊገደዱ ይችላሉ፤ በአንፃሩ ደግሞ...
... በሌሎች አገሮች ደግሞ ሰዎች ባላቸው የጤና ችግር ወይም አካል ጉዳተኝነት ምክንያት አደጋ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ።


... እም... ቀደም ብለው — የሚወዱት ሰው... አሉ
... አንድ ወንድ ሌላ ወንድ ሲወድ ወይም አንዲት ሴት ሌላ ሴት ስትወድ ማለትዎ ነው?
በትክክል!
የበለጠ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ከሞግዚታችሁ ጋር ተነጋገሩ።
ASYLUM
እሺ።
... እም... እዚህ ያሉት መኮንኖች ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በሙሉ እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ?



መኮንኖቹ ስለእናንተ በተቻለ መጠን ለማወቅ ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቋችኋል። ታሪካችሁን አካፍሉ።
ASYLUM
እንዲሁም፣ ከ18 ዓመት በታች የሆነ እና ብቻውን የመጣ ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣናት ወዲያውኑ መንገር አለበት፤ ምክንያቱም ልጆች ከአዋቂዎች የበለጠ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።
ከዚያ፣ ጊዜያዊ ሞግዚት ለእርስዎ ይመደብልዎታል። ጥገኝነት ከጠየቁ በ3 ሳምንታት ውስጥ እርስዎን ለመደገፍ ቋሚ ሞግዚት ይመደብልዎታል።
ከእናንተ ጋር የሚነጋገሩት መኮንኖች ስልጠና የወሰዱ ናቸው እና እናንተን ለማጽናናት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ።
አስፈላጊ ውሳኔዎችን ከማድረጋቸው በፊት ምኞታችሁን ፍላጎታችሁን እና ስጋታችሁን ለመመልከት ይሞክራሉ። እነሱም ሁኔታችሁን በተሻለ ለመረዳት ስለ አገራችሁ ያነባሉ።


ይህም እዚህ ቤተሰብ ያላቸውን ጨምሮ የሁሉንም ሕፃናት የላቁ ጥቅሞች ለማረጋገጥ ነው።
...ነገር ግን በሁሉም ውሳኔዎች ሁልጊዜ ደስተኛ ላትሆኑ ትችላላችሁ።
በቋንቋ ምክንያት የመግባባት ችግር ካለባችሁ፣ አስተርጓሚ መጠየቅ ትችላላችሁ።
የመጨረሻ ነጥብ፣ ጥገኝነት መጠየቅ ለጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ ተብሎም ይጠራል።
ASYLUM
... ከዛስ ምን ይከሰታል?


በሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ትመዘገባላችሁ፤ ፎቷችሁ እና የጣት አሻራዎቻችሁ ይወሰዳሉ እንዲሁም …
ASYLUM
… ሰነዶቻችሁን፣ ስማችሁን፣ የትውልድ ቀናችሁ፣ ስለ ቤተሰባችሁ እና ሌሎችንም ጥያቄዎችን ትጠየቃላችሁ።
መመዝገባችሁ የጥገኝነት ማመልከቻችሁ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ እዚህ እንድትቆዩ ያስችላችኋል።
እርስዎ እዚህ ደህንነትዎ የተጠበቀ ነው
ለመመዝገብ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?
በተቻለ ፍጥነት መመዝገብ አለባችሁ፣ ከ10 ቀናት በማያልፍ ጊዜ ውስጥ።
በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች ለጥገኝነት የሚያመለክቱ ከሆነ እስከ 2 ሳምንታት ሊወስድ ይችላል።


ማመልከቻዬን 'ማስገባት' እንዳለብኝ ተነግሮኛል፣ ያ ማለት ምን ማለት ነው?
አገርሽን ለቀሽ የወጣሽበትን እና መመለስ የማትችይበትን ምክንያት፣ ስለ ጉዞሽ ዝርዝሮች እና የመሳሰሉትን እንድታካፍዪ ትጠየቂያለሽ።
ከአገር ወደ አገር ትናንሽ ልዩነቶች አሉ። በአንዳንድ አገሮች ምዝገባ እና ማስገባት በአንድ ስብሰባ ላይ የሚፈጸም ሲሆን፣ በሌሎች ደግሞ ለየብቻ ይፈጸማል።
ባለሥልጣናቱን ሁለት ጊዜ ካገኙ...
... ከተመዘገባችሁበት ጀምሮ በ21 ቀናት ውስጥ መረጃችሁን በኮምፒውተር ሥርዓት ውስጥ ያስገባሉ። ብዙ ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜ ከመጡ፣ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።
3 x 7 = 2
... እና ከወላጆቻቸው ጋር የሚመጡ ሕፃናት፣ እንደ እድሜያቸው፣ በወላጆቻቸው የጥገኝነት ማመልከቻ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ።


ASYLUM
ሞግዚታችሁን ጥያቄዎች መጠየቅ ትችላላችሁ። ከቤተሰባችሁ ጋር ከሆናችሁ እና ስለ አንዳንድ ነገሮች እርግጠኛ ካልሆናችሁ፣ ከጠበቃ እርዳታ ጠይቁ።
በጠቅላላው ሂደት ውስጥ የሚሰጡት ድጋፍ ከክፍያ ነጻ ናቸው።
ከተመዘገብኩ በኋላ፣ አመልካች መሆኔን የሚገልጽ ሰነድ ተሰጠኝ።
አዎ። ይህ ሰነድ ለጥገኝነት ማመልከታችሁን ያሳያል። አስፈላጊ ነው። ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ አስቀምጡት።
የእኔን ፎቶ አንስቼ በስልኬ ላይ አስቀምጫለሁ...
በጣም ጥሩ!


አቶ ፍሬድ (Mr Fred)፣ አያቴ እዚህ አውሮፓ ውስጥ ናቸው። አሁን አመልካች ስለሆንኩኝ፣ ወደሳቸው ለመጓዝ እችላለሁ?
ገና አይደለም። በተመዘገብክበት ቦታ ቆይ። ባለሥልጣናቱ፣ ከአንተና ከሞግዚትህ ጋር በመሆን፣ እርሳቸውን እንዴት እና መቼ እንደምትቀላቀላቸው ይወስናሉ።
ASYLUM
ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር የመሄድ ትልቅ ውሳኔ ከማድረጋችሁ በፊት፣ መዘዞቹን ለመረዳት ከሞግዚታችሁ ወይም ከጠበቃ ጋር ተነጋገሩ።
...እንዲሁም፣ ብቻችሁን መጓዝ አደገኛ ሊሆን ይችላል!
እዚህ መቆየት እንዳለብኝ ገባኝ።
የጥገኝነት ቃለ-ምልልሳቸውን በሚጠብቁበት ጊዜ ሰዎች የት ነው የሚተኙት እና የሚበሉት?
ባለሥልጣናት መቀበያ ተብሎ የሚጠራ አስተማማኝ እና ተስማሚ መኖሪያ ሊሰጧችሁ ይገባል። ምግብ እና አስፈላጊ ነገሮችን እንዴት ማግኘት እንደምትችሉ ያብራራሉ።


በተለምዶ፣ ከቤተሰብ ጋር ያሉ ልጆች በቤተሰብ መኖሪያ ቤት ይቆያሉ።
የመኖሪያ ማእከል
ብቻቸውን ያሉ ልጆች ተመሳሳይ ሁኔታ ካላቸው ሌሎች ልጆች ጋር ሊቀመጡ ይችላሉ፤ እንደ ፍላጎታቸው መሰረት።
መኮንኖቹ የአካባቢውን ቋንቋዎች የት መማር እንደምትችሉ...
... ትምህርት ቤት መሄድ፣ ሥራ ማግኘት ወይም አስፈላጊ ከሆነ ሐኪም ማየት እንደሚችሉ ያሳውቁዎታል።
ቃለ-ምልልሳችሁን በምትጠባበቁበት ጊዜ እራሳችሁን በሥራ ይያዙ እና ለመዘጋጀት ከጠበቃ ወይም ከሞግዚት እርዳታ ጠይቁ።
የተጨነቁ፣ የተወጠሩ ወይም የፈሩ እንደሆነ ከተሰማችሁ፣ ለሚተማመኑበት ሰው ንገሩ። መኮንኖቹ ሊረዷችሁ የሚችሉት ምን እንደሚያስጨንቃችሁ ካወቁ ብቻ ነው።
ASYLUM


እርስዎ፣ ሞግዚትዎ ወይም ተንከባካቢዎ ስለ ቃለ-ምልልሱ ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ የሚገልጽ የጽሁፍ ግብዣ በኢሜል ወይም በፖስታ ይደርሳቹሃል።
01/04
14h30
ሕፃናት ከወላጅ ወይም ከሞግዚት ጋር ኃላፊነት ካለበት አዋቂ ጋር ሆነው ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለባቸው።
በዚያ ቀን ከታመምኩ ምን ይከሰታል?
አንተ ወይም ሞግዚትህ ለባለሥልጣናት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባችሁ።
እም… በጥገኝነት ቃለ-ምልልስ ወቅት ምን ይከሰታል?
በቃለ-ምልልሱ ወቅት 'የጉዳይ መኮንን' ወይ ኦፊሰር የተባለ ሰው…
…ስለ ቤተሰባችሁ፣ በቤታችሁ ስላለው ሕይወት፣ ስላለው የደህንነት ሁኔታ፣ ለምን እንደመጣችሁ እና ስለ ጉዟችሁ ጥያቄዎችን ይጠይቋቹኋል። የምትናገሩት ነገር ሁሉ ምስጢራዊ ነው፣ ይህም ማለት ከማንም ጋር አይጋራም።


እም... እነዚህን ነገሮች ሁሉ ማስታወስ ወይም ማሰብ ቀላል አይደለም...
አውቃለሁ፣ ከባድ ነው። ነገር ግን መኮንኖቹ የሰለጠኑ ናቸው እና ይረዷቹኋል።
አንድ ሰው ልክ እንደ ፈተና ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ ብሎ ነግሮኛል።
ከሞግዚታችሁ ወይም ከጠበቃችሁ ጋር ለመዘጋጀት ሞክሩ።
እኔ እችላለሁ። ቃለ-ምልልሱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?
ASYLUM
በተለይም ተርጓሚ ካለ፣ ትንሽ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ከደከማችሁ የእረፍት ጊዜ መጠየቅ ትችላላችሁ።
ጥያቄን መመለስ ካልቻልኩስ?
የቻልከውን ሁሉ ሞክር። አንዳንድ ዝርዝሮችን ከረሳህ፣ እንደረሳሀው። የቻልከውን ያህል አካፍሉ። በትክክለኛ ቀናቶች ፈንታ፣ በጋ ወይም የበዓል ጊዜ እንደነበረ መናገር ትችላለህ።
ፈጽሞ ነገሮችን ፈጥረው አይናገሩ።


በመጨረሻ፣ መኮንኑ መልሶችዎን ከእርስዎ ጋር ያጣራል። በትክክል ያልተረዱት ነገር ካለ፣ እንዲያስተካክሉት ይጠይቋቸው። በኋላ ላይ ለውጥ ማድረግ ከባድ ነው።
ታሪኬን ለመደገፍ ደብዳቤዎችን፣ የትምህርት ቤት ወይም የህክምና ሪፖርቶችን እና የጋዜጣ ጽሑፎችን ማምጣት እችላለሁ?
በትክክል!
ASYLUM
...እሺ፣ ከጓደኞች ወይም ከቤተሰብ የተሰጡ መግለጫዎች፣ ወይም እንደ የልደት የምስክር ወረቀቴ ያሉ የሰነዶች ፎቶዎችስ?
አዎ፣ ታሪካችሁን እና ለምን መሰደድ እንደነበረባችሁ ለማስረዳት ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ።
ጓደኞች እና ቤተሰብ ይህን መረጃ እንዳገኝ ሊረዱኝ ይችላሉ።
አዎ፣ ነገር ግን ራሳቸውን ለአደጋ እንዳይጥሉ መጠንቀቅ አለባቸው። ባለሥልጣናቱ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚፈልጉ ንገሩዋቸው።
ባለሥልጣናቱ መረጃው ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚረዳቸው ከሆነ፣ ቃለ-ምልልስዎን ቀጠሮውን እንደገና ሊያዘጋጁት ይችላሉ።
አንድ ጓደኛዬ ባለሥልጣናት የጥገኝነት ማመልከቻውን እንደማይገመግሙት ነግሮኛል። ይህ ለምን ሆነ?
ባለሥልጣናቱ በመጀመሪያ የጥገኝነት ማመልከቻ መመርመር ያስፈልጋቸው እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ያጣራሉ።


በሌላ አገር ጥበቃ አስቀድማችሁ ካገኛችሁ ወይም ደህና ነው ብለው ከሚያስቡት አገር የመጣችሁ ከሆነ ይህን ላያደርጉ ይችላሉ።
ASYLUM
አቶ ፍሬድ፣ አንድ ሰው መመለስ እየፈለገ ግን መመለስ ካልቻለስ—ምናልባት ስለፈራ ወይም ጥያቄዎቹ በጣም ግላዊ ስለሆኑ?
ያ የተለየ ነው። ሰዎች የሚሸሹት በጣም መጥፎ ተሞክሮዎች ስላጋጠማቸው ነው። ስለ እሱ ማውራት አለመፈለግ ተፈጥሯዊ ነው።
ቢሆንም፣ በጣም የሚያሳዝን ቢሆንም ወይም አሳፋሪ ቢመስልም፣ የቻላችሁትን ያህል ለማካፈል ሞክሩ። ልታፍሩበት የሚገባ ምንም ነገር ሊኖር አይገባም። ለማስታወስ ከተቸገራችሁ ወይም ምን ማጋራት እንዳለባችሁ እርግጠኛ ካልሆናችሁ፣ ንገሩዋቸው።


ያጋጠማችሁ ነገር አስፈላጊ መረጃ ሊሆን ይችላል። መኮንኖቹ እናንተን ለማጽናናት ይሞክራሉ። እየተቸገራችሁ እንደሆነ ካዩ፣ ቆም ሊሉ ወይም እናንተን ለመደገፍ አንድ ሰው እንዲቀላቀላችሁ ሊጠይቁ ይችላሉ።
እዚህ የሚሠሩ ሁሉም ሰዎች በአክብሮት ሊይዟችሁ ይገባል። ይህን ካላደረጉ፣ በይፋ ቅሬታ ማቅረብ ትችላላችሁ—እርስዎን የሚረዳዎትን የሚተማመኑበትን ሰው ይጠይቁ።
የአንድ ጓደኛዬ የግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልሱ ቆሞ ሐኪም እንዲያይ ተጠየቀ። ለምን?
እም... ዝርዝሩን አላውቅም...
አንዳንድ ጊዜ፣ መኮንኑ ውጤቱ ለጥገኝነት ማመልከቻው ይረዳል ብሎ ካሰበ፣ አንድ ሰው የሕክምና ምርመራ እንዲያደርግ ሊጠየቅ ይችላል።


ምናልባት ሰውዬው ከዚህ በፊት ያልተመዘገበ እና ሕክምና የሚያስፈልገው የጤና ወይም የአእምሮ ጤና ችግር ሊኖረው ይችላል። በውጤቶቹ ላይ በመመስረት፣ ቀጣይ እርምጃዎች ይወሰናሉ።
መኮንኖቹ ምርመራውን ለማድረግ መስማማታችሁን ይጠይቋችኋል። እንደ ህጻን ልጅ መጠን፣ ወላጃችሁ ወይም ሞግዚታችሁ ይሳተፋሉ።
ASYLUM
እም... ጥገኝነት እንደተሰጠኝ ወይም እንዳልተሰጠኝ እንዴት አውቃለሁ?
ከቃለ-ምልልሱ በኋላ፣ መኮንኖቹ ሁሉንም መረጃዎች ይገመግማሉ እና በማመልከቻዎ ላይ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ። ውሳኔውን የሚገልጽ ደብዳቤ ለመቀበል ጊዜ ሊወስድ ይችላል።
ገብቶኛል። ለዚህ ነው ሊያገኙኝ እንዲችሉ የተሻሻለ ስልክ ቁጥሬንና አድራሻዬን የፈለጉት።
አድራሻ
ኢሜል
ስልክ


አዎ! ውሳኔው አዎንታዊ ከሆነ፣ ሰዎች መቆየት ይችላሉ እንዲሁም የጥበቃ ዓይነት ያገኛሉ።
ይህ የስደተኛነት ደረጃ ሊሆን ይችላል?
አዎ! ...ወይም አማራጭ ጥበቃ።
በሁለቱም ሁኔታዎች፣ ጥበቃ እስከሚያስፈልጋችሁ ጊዜ ድረስ እዚህ ለመቆየት የመኖሪያ ፈቃድ ታገኛላችሁ። ጠበቃ ዝርዝሩን ሊያስረዳችሁ ይችላል።
ውሳኔው አሉታዊ ከሆነ፣ ወደ ትውልድ አገርዎ ወይም ቀደም ብለው ወደኖሩበት አገር መመለስዎ ደህና እንደሆነ ስለተወሰነ መቆየት አይችሉም ።
ይግባኝ
ካልተስማማችሁ፣ ይግባኝ ማለት ትችላላችሁ፣ ይህም ጉዳያችሁ እንደገና እንዲታይ መጠየቅ ማለት ነው።


ይግባኝ ለማለት የተወሳሰበ ነው?
ትንሽ።
ቅጾቹን ወዲያውኑ መሙላት ይኖርባችኋል። እርዳታ ለማግኘት ጠይቁ። አስታውሱ፣ ይግባኝ ማለት ግምገማ ወይም ዳግም እንዲታይ ብቻ እንጂ ጥበቃ እንደምታገኙ ዋስትና አይሰጥም።
ሁላችሁም በጣም ደክሟችኋል፣ ለዛሬ እዚህ እንቋጭ።
ሌላ አንድ ጥያቄ... መኮንኖች ስለ ድንበር እና መመለስ ሂደት ሲያወሩ ሰምቻለሁ...
ASYLUM



የመመለስ ሂደት አገራቸው ደህና እንደሆነ ስለሚቆጠር መመለስ ላለባቸው ሰዎች ነው።
አንዳንድ ሰዎች በፈቃደኝነት ለመመለስም ሊመርጡ ይችላሉ። ድጋፍ ለማግኘት ለመኮንኖቹ አሳውቁ።
የድንበር ሂደት ማለት የጥገኝነት ማመልከቻችሁ በአየር፣ በመሬት ወይም በባህር በደረሱበት ቦታ ይመረመራል ማለት ነው።
ጉዳይዎ እስኪወሰን ድረስ እዚያ መቆየት ሊኖርባችሁ ይችላል እና በነጻነት መንቀሳቀስ አትችሉም።
ከቤተሰብ ጋር የሚመጡ ልጆች ከ3 እስከ 4 ወራት በሚቆየው በድንበር ሂደት ውስጥ ሊቆዩ ይችላሉ።
ብቻቸውን የሚመጡ ልጆች ወደ ድንበር ሂደት አይገቡም፤ ሆኖም ጥቂት ልዩ ሁኔታዎች አሉ።
የበለጠ ለማወቅ ከሞግዚታችሁ ጋር ተነጋገሩ።



አንድ የመጨረሻ ጥያቄ... አንድ ልጅ ትንሽ ለመምሰል ወይም በዕድሜ ለመጨመር ስለ ዕድሜው ከዋሸ ምን ይከሰታል?
ሁልጊዜ ትክክለኛ ዕድሜያችሁን ለመኮንኖቹ ተናገሩ ጥርጣሬ ካደረባቸው፣ የእድሜ ምዘና ሊጠይቁ ይችላሉ።
ከምሳ በኋላ ከወይዘሮ ኢነስ ጋር ስለ እድሜ ምዘና እንነጋገራለን። ስለእሱ ማወቅ ለእናንተ አስፈላጊ ነው።
አዎ፣ እንብላ፣ ሆዴ እያጉረመረመ ነው!
አመሰግናለሁ!
ምንም አይደለም! ከምሳ በኋላ በዛፉ ስር ባለው ጠረጴዛ ላይ እንገናኝ።
ASYLUM

# አስፈላጊ

## በዚች ሀገር...

እኔን የመመዝገብና የግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልሴን የማደራጀት ኃላፊነት ያለበት ባለሥልጣን የሚከተለው ነው፡-

______________________________

የሞግዚቴ ስም፡ ______________________________

______________________________

ስለ ጥገኝነት ሂደት የበለጠ ለመማር እና ለቃለ-ምልልሴ ለመዘጋጀት ጠበቃን በነጻ ማግኘት እችላለሁ።

ለዚህም፣ የሚከተለውን ማግኘት እችላለሁ፡- ______________________________

______________________________

ስለ የጥገኝነት ማመልከቻዬ በተሰጠው ውሳኔ ባልስማማ፣ እንዴት ይግባኝ ማለት እንዳለብኝ ምክር ለማግኘት ሞግዚቴን እና ጠበቃዬን ማግኘት እችላለሁ።

ይግባኝ ለማለት የሚከተለው መረጃ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡- ______________________________

______________________________

______________________________

እዚህ የሚሰሩ ማንኛውም ሰዎች፣ እንደ መኮንኖች፣ የሕግ አማካሪዎች፣ ማህበራዊ ሰራተኞች ወይም ሞግዚቴ መጥፎ አድርገው ከያዙኝ፣ ቅሬታ ማቅረብ እችላለሁ እና የሚከተለውን ማግኘት እችላለሁ፡- ______________________________

______________________________

የአደጋ ጊዜ ከሆነ፣ አምቡላንስን በ ______________________________
ወይም ፖሊስን በ ______________________________ ማግኘት እችላለሁ።

ወደ ትውልድ አገሬ በፈቃደኝነት ለመመለስ ከፈለግኩ፣ ሞግዚቴ ዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት (International Organization for Migration፣ IOM) ጋር እንድገናኝ ይረዳኛል።

______________________________

የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ (United Nations Refugee Agency፣ UNHCR) በሕግ ነክ ጉዳዮች ላይ እኔን ወይም ቤተሰቤን ድጋፍ ሊሰጠን ይችላል። የUNHCR የመገናኛ መረጃ፡-

______________________________

ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፡ ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

# አጭር ፈተና

**ስለ ጥገኝነት ሂደት ያለኝን እውቀት እየፈተሽኩ ነው።**

ትክክለኛውን መልስ ምልክት ያድርጉበት።

1. ሰዎች ዓለም አቀፍ ጥበቃ ወይም ጥገኝነት የሚጠይቁት ወደ አገራቸው ለመመለስ ስለሚፈሩ ነው፣ እዚያ እነሱ ወይም ቤተሰባቸው ደህንነታቸው አይጠበቅም።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

2. ባለሥልጣናት ጥገኝነት ከጠየቅሁበት ጊዜ አንስቶ ከ5 እስከ 8 ቀናት ውስጥ እኔን መመዝገብ አለባቸው። ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ፣ እስከ 2 ሳምንታት ሊወስድ ይችላል።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

3. ጥገኝነት ከጠየቅኩ በኋላ ወደምፈልገው ማንኛውም አገር መጓዝ እችላለሁ።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

4. በግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልሴ ወቅት ከሚጠይቁኝ መኮንኖች ጋር አብሮ መሥራት አስፈላጊ ነው። አንድ ነገር ካላስታወስኩ፣ ልነግራቸው እችላለሁ።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

5. ብቻቸውን የሚመጡ ልጆች ወደ ድንበር ሂደት አይገቡም።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

6. ስለ ግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልስ ጥያቄዎች ካሉኝ፣ ሞግዚቴን ወይም ጠበቃን መጠየቅ እችላለሁ። የእነሱ ድጋፍ በነፃ ነው።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

7. መኮንኖች በግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልስ ወቅት የሚሰበስቡትን መረጃ ከእኔ ጋር ያረጋግጣሉ፤ ስለዚህ ስህተቶችን ማስተካከል እችላለሁ።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

8. ለግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልሴ በቀጠሮው መቅረብ ካልቻልኩ ምንም ችግር የለውም።
   - a. እውነት
   - b. ሐሰት

# አጭር ፈተና

9 ያሉኝን ሰነዶች በሙሉ ለመኮንኖቹ ማጋራት ጥሩ ነው፣ በስልኬ ላይ ያሉት የሰነዶቹ ፎቶግራፎች ብቻ ቢሆኑም እንኳ።

- ○ a. እውነት
- ○ b. ሐሰት

10 ከግል የጥገኝነት ቃለ-ምልልስ በኋላ፣ መኮንኖች ሁሉንም መረጃዎች ይመለከታሉ እና ጥበቃ እንደሚያስፈልገኝ ወይም እንደማያስፈልገኝ ይወስናሉ።

- ○ a. እውነት
- ○ b. ሐሰት

11 ከውሳኔያቸው ጋር ካልተስማማሁ፣ ከምግዚቴ ወይም ከጠበቃ ጋር ተነጋግሬ ውሳኔውን መቃወም (ይግባኝ ማለት) እችላለሁ።

- ○ a. እውነት
- ○ b. ሐሰት

## የጥያቄዎች መልሶች

ጥያቄ 1: a; ጥያቄ 2: a; ጥያቄ 3: b; ጥያቄ 4: a; ጥያቄ 5: a; ጥያቄ 6: a።
ጥያቄ 7: a; ጥያቄ 8: b; ጥያቄ 9: a; ጥያቄ 10: a; ጥያቄ 11: a።

# ማስታወሻዎች

## AMHARIC

ይህ ቡክሌት ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ ቡክሌት ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ የተፈቀደው ለአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ብቻ ነው። የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ወይም በሌላ ማንኛውም ኃላፊነት ባለው ሶስተኛ ወገን በዚህ ቡክሌት ውስጥ የተካተተው መረጃ ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ሙሉነት፣ ሕጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ላይ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይቀበልም። ይህ ቡክሌት ሊውልበት ስለሚችል ጥቅም የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅትም (EUAA) ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025

